
ስርዓተ-ጾታን የሚያስተናግድ የትምህርት አሰጣጥ

ታኅሣሥ 2015

Trainee Self Introduction



Tell a brief personal background of yourself the occasion that you expect from this Training to the person near to you & let him introduce you to the participants

5 Minute

ይዘት

- መግቢያ
- ክፍለ አንድ፡- ስርዓተ-ጾታን መረዳት
- ክፍል ሁለት፡- የስርዓተ-ጾታን የሚያስተናግድ ትምህርት ቤት
- ክፍል ሦስት፡- ስርዓተ-ጾታን የሚያስተናግድ የትምህርት አሰጣጥ
- ክፍል አራት፡- ስርዓተ-ጾታን የሚያስተናግድ የትምህርት ዕቅድ

የስልጠናው ዓላማ

- ከተሳታፊዎች አውድ አንጻር ተገቢ የሆኑ የስርዓተ - ጾታ ጉዳዮችን መለየት
- ስርዓተ - ጾታን ያማከለ የትምህርት አሰጣጥ መሰረታዊ ጉዳዮችን መረዳት
- ሰልጣኞች የስርዓተ - ጾታን ጉዳዮች እንዴት በትምህርት ቤት ደረጃ ትኩረት እንዲሰጣቸው ማድረግ እንዲችሉ መርዳት

መግቢያ



Reflection and Discussion on the topic

ሀ) በአዋቂ ወንዶችና በሴቶች እንዲሁም በህጻናት ሴቶችና ወንዶች የሚሰሩ ስራዎችን ዘርዝሩ። ይህ ፍትሃዊ የስራ ክፍፍል ነው ብላችሁ ታምናላችሁ?

ይህ ሴቶችን በማስተማር ላይ የሚኖረውን አንድምታ ተወያዩ።

ክፍል አንድ

ስርዓተ - ጾታን መረዳት

ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ጽንሰ ሃሳቦች ስለ ስርዓተ-ጾታ ትክክለኛ ግንዛቤ ለመያዝ ይረዳሉ።

1. **ጾታ መድሎና ማግለል:-**ማንኛውም የሴቶችን እውቅና፣ እንቅስቃሴ ወይም ነጻነት የሚያግድ ጾታን መሰረት ያደረገ መድሎ፣ ማግለል ወይም ማዕቀብ ነው።
2. **የጾታ እኩልነት፡-** ማንኛቸውም አይነት በሴቶች ላይ በጾታቸው ምክንያት የሚከሰቱ የአድሎና መገለል መገለጫዎችን ማስቀረትና ወንዶችና ሴቶች እኩል መብት፣ ግዴታና መልካም አጋጣሚዎች እንዲቋደሱ ማድረግ።
3. **ስርዓተ-ጾታዊ ፍትህ፡-** ወንዶችና ሴቶች ጥቃቅን ጥቅሞችን፣ ሃላፊነትን፣ እና መልካም አጋጣሚዎችን በፍትሃዊነት እንዲቋደሱ ማድረግ ነው።
4. **ስርዓተ-ጾታዊ ግንኙነት፡-** ሴቶችና ወንዶች በግል፤ በማህበራዊ መስተጋብርና በልሎችም ግንኙነቶች ውስጥ በእኩልነት ለሃላፊነት የሚበቁባቸው፤ የሃላፊነት ቦታዎችን የሚይዙባቸው እና ቁሳዊ ሃብት የሚያገኙባቸው ሁኔታዎች እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚሰጣቸውን አክብሮትና ቦታ ይመለከታል።
5. **የተዛባ የስርዓተ-ጾታ አመለካከት፡-** ለወንድም ሆነ ለሴት ተገቢ ነው በሚል በማህበረሰቡ ዘንድ በሰፊው ተቀባይነት ያገኘ የወንድ ወይም የሴት ባህሪ ወይም ስራ የሚባል የተሳሳተ ግንዛቤ።

የቀጠለ..

- **ስርዓተ-ጾታዊ ዝምታ፡ -** ጾታዊ ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ አለማስገባት። ይህም የተለየ የሴቶች ልጆች ፍላጎት ግምት ውስጥ እንዳይገባና አድሎ እንዲፈጸምባቸው የሚያደርግ፤ አመለካከት።
- **የስርዓተ-ጾታ እውርነት ወይም ደንታቢስነት፡ -** አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ በጾታዎች መካከል ልዩነት እንዳለ አለመገንዘብ ወይም እውቅና አለመስጠት፤
- **ለስርዓተ-ጾታ ስሱ:-** ስርዓተ-ጾታን መሰረት ያደረገ አድሎና መገለልን የሚያስከትሉ ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ የማስገባት አቅም
- **የስርዓተ-ጾታ ግንዛቤ፡ -** በግልጽ በገሃድ ባይታዩም እንኳ የጾታ እኩልነትን የሚያዛቡና አድሎና ስርዓተ- ጾታን መሰረት ያደረጉ አድሎና መገለል የሚያስከትሉ ጉዳዮችን የመለየት ችሎታ።
- **ስርዓተ-ጾታን ማማከል:-** ጾታዊ እኩልነትና የስርዓተ-ጾታዊ ፍትህን ለማስፈን የተዛባ የስርዓተ-ጾታ አስተሳሰብ፣ አድሎና መገለልን ለማስቀረት መስራት
- **አቅም ማጎልበት:-** የተረሱ የህብረተሰብ ክፍሎች፤ ለምሳሌ ድሆች፣ አናሳዎችንና ሴቶች የሚደርስባቸውን አድሎና መገለል እንዲገነዘቡ በማድረግ የሚደርስባቸውን ተጽዕኖ እንዲቋቋሙና እንዲወጡት ማድረግ ወይም ማስቻል፤
- **የስርዓተ-ጾታን ማህበራዊ ስሪት መረዳት:-** ስርዓተ-ጾታ በተለያዩ ደረጃዎች ባሉ የተለያዩ መዋቅሮች የሚገለጽ ማህበራዊ ስሪት ነው።

የቀጠለ..

- **ቤተሰብ፡ -** ሴቶችና ወንዶች የተለያየ ስራ፣ መብትና ሚና አላችው። ይሄ የሚጀምረው ገና በትንሽነታቸው ሲሆን በውርስና በሃብት ክፍፍል ላይ ተጽእኖ አለው።
- **ማህበረሰብ፡ -** ማበራዊ ስሪት የሆኑ ሚናዎች ለወንዶችና ለሴቶች የተለያየ ሚና፣ መብትና ጥቅማ ጥቅም በመስጠት ይጠናከራሉ። በማህበራዊ ስብሰባዎች ሴቶች እንዲያበስሉና እንዲያስተናግዱ ሲደረግ ወንዶች ደግሞ እንዲወያዩ እና እንዲወስኑ ይደረጋል።
- **ትምህርት ቤት፡ -** መምህራን የተዛቡ የስርዓተ-ጾታ አስተሳሰቦችን የሚያጎለብቱ ስርዓተ ትምህርትና የአመራር ስልት በመጠቀም ወንዶችንና ሴቶችን በልዩነት ያያሉ። መምህራን ወንዶችን ብቻ ሊያበረታቱ ወይም ደግሞ ለሴቶች አትኩሮት ላይሰጡ ይችላሉ።

የቀጠለ..

- **መንግስት፡ -** ስርዓተ-ጾታን ያማከለ ዕቅድና ፖሊሲ በተለያዩ የመንግስት የስራ ዘርፎችና ደረጃዎች አለመኖር፣ በሁሉም ደረጃዎች የስርዓተ-ጾታ ግንዛቤ እንዲሰፋ አለመስራት፣ ያሉትን ፖሊሲዎችም ቢሆን በተግባር ለማዋል የዕውቀትና የፍላጎት አለመኖር።
- **ብዙሃን መገናኛ፡ -** ሚዲያው የጾታ እኩልነት እንዲከበር እየሰራ አይደለም። እንዲያውም የተዛባ የሴቶችና የወንዶች ምስል እንዲኖር በማድረግ የጾታ እኩልነት እንዳይሰፍን ትልቅ ሚና እየተጫወተ ነው።

ክፍል 2፡– ስርዓተ-ጾታን የሚያስተናግድ ትምህርት ቤት

- **ስርዓተ-ፆታን የሚያስተናግድ ት/ቤት ማለት በእለት ተእለት የትምህርት እንቅስቃሴ እንዲሁም በማህበራዊና በቁስ አካላዊ አውድ ውስጥ የወንዶችንና የሴቶችን ልዩ ፍላጎት የሚገነዘብና በተግባር የሚያሳይ ማለት ነው።**

ከእነዚህም መካከል የሚከተሉት ማሳያዎች ናቸው፡-

- የማስተማር ስራው፣የመምህር - ተማሪ ግንኙነት፣ የትምህርት ቤቱ አመራር፣ የትምህርት ቤቱ ዲዛይን፣ ያለው መሰረተ ልማትና የመሳሰሉት የትምህርት ቤት አካላት የተወሰኑ ማሳያዎች ናቸው።
- የመማሪያና ማስተማሪያ ጽሁፎቹ የተዛባ የስርዓተ - ጾታ አመለካከት ያካተቱ ሊሆኑ ይችላሉ።

የቀጠለ..

- መምህራን በጾታቸው ምክንያት ለሴቶችና ለወንዶች ስለሚያስፈልጉዋቸው ጉዳዮች የስርዓተ-ጾታ ግንዛቤ ደንታ ቢስነት ሊያሳዩ ይችላሉ።
- የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ጾታዊ ትንኮሳዎችንና ጥቃቶችን በበቂ ሁኔታ የሚቆጣጠርበት የአመራር ስልት ላይኖረው ይችላል።
- ትምህርት ቤቶች ለወንዶችና ለሴቶች የተለያዩ የመጸዳጃ ቤቶች ላይኖራቸው ይችላል።
- ተማሪዎች ጾታዊ ጥቃቶች ምን ያህል ጎጂ እንደሆኑና ሲከሰቱም ምን ማድረግ እንዳለባቸው ግንዛቤ ላይኖራቸው ይችላል።
- ይህም ትምህርት ቤቱ ስርዓተ-ጾታን ያማከለ እንዳይሆን እና የተሳለጠ የመማር ማስተማር ሥራ እንዳይካሄድ ሊያደርገው ይችላል።

ክፍል 3፡– ስርዓተ–ፆታን የሚያስተናግድ የትምህርት አሰጣጥ

- ስርዓተ-ፆታን የሚያስተናግድ የማስተማር ስልት ማለት ለወንድና ሴት ተማሪዎች ልዩ ትምህርታዊ ፍላጎት አፅንኦት የሚሰጥ የመማር- ማስተማር ሂደት ነው።
- ለመምህራን ስርዓተ-ፆታን የሚያስተናግድ የማስተማር ስልት ማለት መምህራን በሁሉም የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች ማለትም የትምህርት ቅፅ በሚወጣበት በማስተማርና የትምህርት ምዘና በሚካሄድበት ጊዜ ሁሉ ለስርዓተ-ፆታ ጉዳይ አፅንኦት መስጠት ማለት ነው።

የቀጠለ..

- የክፍል ውስጥ ተግባራት ምልከታ እንደሚያሳየው መማርና ማስተማር በአብዛኛው ለአንድ ፆታ ያደላ ነው። ብዙ መምህራን ወንድና ሴት ተማሪዎች በእኩልነት እንዲሳተፉ እድል የማይሰጡ የማስተማሪያ ስልቶችን ይተገብራሉ። የሚጠቀሙባቸውም የትምህርት መረጃዎችና መሳሪያዎች የቆየውን የተዛባ የፆታ አመለካከት የሚያስቀጥሉ ሲሆኑ ይህም ሁኔታ ስርዓተ-ፆታን የሚያስተናግድ የማስተማሪያ ዘዴን ተግባራዊ ማድረግን ግድ ያደርገዋል።

ክፍል 4፡– ስርዓተ–ፆታን የሚያስተናግድ የትምህርት ፅቅድ

- የትምህርት እቅድ የትምህርት መረጃ መሳሪያ አጠቃቀምን፣ የትምህርት ይዘትን፣ የማስተማር ስልትንና የቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ በዝርዝር ዝግጅት የሚደረግበት ነው። በክፍል ውስጥ የሚኖረው የተማሪ አስተማሪ ግንኙነት የክፍል ውስጥ አቀማመጥ፣ የትምህርቱ ምዘና የትምህርት እቅድ አካላት ናቸው።
- **የማስተማሪያ መሳሪያዎች፡–** በመማሪያና ማስተማሪያ ቁሳቁሶች ውስጥ ያለውን የቋንቋ አጠቃቀም ስርዓተ-ፆታን ከማስተናገድ አንፃር መፈተሽ ይገባል፣
- **የማስተማሪያ ዘዴ፡–** በተቻለ መጠን ወንድና ሴት ተማሪዎችን እኩል ሊያሳትፉ የሚችሉ የማስተማሪያ ዘዴዎችን መምረጥ

የቀጠለ...

- በተቻለ መጠን ወንድና ሴት ተማሪዎችን እኩል ሊያሳትፉ የሚችሉ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ምረጥ/ምረጭ
- **የስርዓተ-ፆታ ውሱንነት ጉዳዮች፡-** ክፍል ውስጥ ስርዓተ-ፆታን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ለማየት ጊዜ ይኑህር/ይኑርሽ።
- **ግብረ-መልስ፡-** ወንድና ሴት ተማሪዎች ትምህርቱ እንደገባቸው ለማረጋገጥ ለወንድና ለሴት ተማሪዎች ተገቢ ግብረ-መልስ በማዘጋጀት ስጥ/ስጭ።


tea
TiME